## ???-? ?? ? ????? 

## *የፀጋ (የመንፈስ ቅዱስ) ስጦታዎችን መረዳት (ክፍል ሦስት)*

***መጠናት ያሉባቸዉ ጥቅሶች***
ሮሜ 12፡7-8፣ 1ቆሮ 12፡28፣ ኤፌ 4፡11
***መግቢያ፡***

በዚህ ሳምንት ከመንፈስ ስጦታዎች 3ቱን ወስደን እንወያያለን

- እያንዳንዱን የፀጋ ስጦታ በምንወያይበት ጊዜ እግዝአብሔር ላንተ የሰጠውን የፀጋ ስጦታ መንፈስ ቅዱስ እንዲያረጋግጥልህ አጥብቀህ ፀልይ።
- እግዚአብሔር በመንፈሱ ያረጋገጠልህን መንፈሳዊ (የፀጋ) ስጦታ(ዎች) የክርስቶስ አካል እንዲገነባ/እንዲታነፅ ቤተክርስቲያንን ለማገልገል እንዲዉል ውሳኔ ማድረግ አለብህ።
- የፀጋ ስጦታህን ለጌታ አገልግሎት ስታውል፣ እግዚአብሔር ያቀደውን ሥራ በአካሉ ውስጥ ይሰራል።
- አንተም ለጌታ የመገልገልያ መሳሪያ ስለሆንክ እግዚአብሔር ህይወትህን ይበርካል።
- የፀጋ ስጦታ በህይወትህ ኑሮ ፍሬ ካላፈራህበት - በመጨረሻ የሚጠብቃህ ፍርድ ነው (ማቴ 7፡15-23)።

1. የአመራሪ ወይም የአስተዳደር ስጦታ (ሮሜ 12፡7)
    - ይህ የፀጋ ስጦታ - መሰራት የለብትን ሥራ እየሰሩ ሌሎች ሰዎችም እንዲሰሩ የማድረግ ችሎታ ነው።
    - ይህ የፀጋ ስጦታ ስኖረን እንደጌታ ፈቃድ ግቦችን የማቀድና ተፈፀምናትን እንዲያገኙ የማድራግ ችሎታ ነው።
    - በተጨማሪ አስቸጋር ለሆኑ ነገሮች መፍትሔን ማግኘትና ቆራጥ ውሳኔን የማድረግም ስጦታ ነው።
    - ይህ የፀጋ ስጦታ በእኛ ህይወት መኖሩን የምንለካበት መመዘኛዎች፡
        - ➢ በሌሎች ዉስዋ ለአገልግሎት የሚያበቃውን ችሎታ ማየትና ሰዎችን ለሥራ ማነቃቀት እችላለሁ፡፡
        - ➢ ሌሎች ሰዎች ይከተሉኛል።
        - ➢ ነገሮችን ማደራጀትን ሃላፊነትን መውሰድ እችላለሁ።
        - ➢ ችግሮች ስያገጥሙ በተለያየ ሁኔታ መፍትሔ የሆኑ ሀሳቦችን እየቀረብኩ ችግሮችን እፈታሉ።
        - ➢ አስቸጋር የሆኑ ውሳኔ መወሰን ስያስፈልግ ሳላመነታ ለመወሰን እችላለሁ።
        - ➢ ለሌሎች ሀላፊነትን መስጠት ስኖርብኝ፣ አራሴ ብቻ ለመስራት ከመሞከር ሌሎች እንዲሳተፉ አደርጋለሁ ።
    - ማስተዋል የሚገቡን ነገሮች፡-
        - ➢ ሰዎች እኛ በልነው መንገድ ብቻ እንዲሄዱ መጨን የለብንም።
        - ➢ ሰዎች ብቻ ማሰራት ሳይሆን፣ እራሳችንም መስራት እንደለብኝ ማስተዋል አለብን።
        - ➢ ሰዎች ሀሳባችንን ሳይቀበሉ ቢቀሩ መዘንና የግል ጉዳይ ማድረግ የለብንም።
        - ➢ መሪ መምራት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ለመመራት ፍቃደኛ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ቁጭ በሉ ሲለን ተቀምጠን በሌሎች ለመመራት ፍቃደኛ መሆን ያስፈልጋል።

2. ማበረታታት ወይም የመምከር ስጦታ (ሮሜ 12፡8)
    - ይህ የፀጋ ስጦታ ሰዎችን የመፅናናትና የማደፋፈር፣ እንዲሁም ትክክለኛ ኑሮ እንዲኖሩ የማነቃቀት ልዩ ችሎታ ነው።
    - በተጨማሪ የሰዎችን ችግር አይተው ውሰኔ እንዲያደርጉ የመምከር ችሎታ ነው። (1 ተሰ 2፡11-12፣ 1ተሰ 5፡14)
    - ይህ የፀጋ ስጦታ በእኛ ህይወት መኖሩን የምንለካበት መመዘኛዎች፡
        - ➢ ሌሎች ሰዎች በችግራቸው መውሰድ የሚገባቸውን ትክክለኛ እርምጃ የመረዳት ችሎታ አለኝ።
        - ➢ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለምክር (ለመፅናናት) ይቀርቡኛል።
        - ➢ የተጨነቁት ሰዎችን በግል አግኝቼ ማበረታታት፣ መፅናናት እወዳለሁ።
        - ➢ በቃልና በተግባር ሰዎች ወደ መታዘዝ በረከት እንድቀርቡ ማነቃቀት እችላለሁ።
    - ማስተዋል የሚገቡን ነገሮች፡
        - ➢ ሰዎችን መምከር፣ ማባበል እንዳልሆነ ማስተዋል አለብን።
        - ➢ ሰዎችን ስንመክር በሎላ ሰው ህይወት ጣልቃ እንዳንገባ መጠንቀቅ ይኖርብናል።
        - ➢ የምንመክረው ምክር በእግዚአብሔር ቃል መደገፍ አለበት።
        - ➢ ሰዎች ምክራችንን ተቀብለው እራሳቸው እርምጃ ይውሰዱ እንጂ፣ መስገደድ የለብንም።
3. የማስተማር ስጦታ (ሮሜ 12፡7፣ 1ቆሮ 12፡28፣ ኤፌ 4፡11)
    - ይህ ስጦታ ስኖረን የእግዚአብሔርን ቃል የመረዳትና የማስተዋል ልዩ ችሎታ ይኖረናል።
    - በተጨማሪ ጤናማ የሆነ ትምህርትን ሌሎችን የማስተማሪና የማካፈል ችሎታ ይኖረናል።
    - እንዲሁም ግልጽ የልሆኑ፣ ከባድ የሚበሉ የመፅሀፍ ቅዱስ ሃሳቦችን ሰዎች በሚረዱበት መንገድ የማስረዳት ችሎታ ነው።
    - ይህ የፀጋ ስጦታ በእኛ ህይወት መኖሩን የምንለካበት መመዘኛዎች፡
        - ➢ በመፅሐፍ ቅዱስ እውነተኛቱናትና በእርሱም ውስጥ ላለው ስልጣን ህይወቴን አስገዛለሁ።
        - ➢ ቃሉን ለማጥናትና ለማስተማሪ ራሴን ለማዘጋጀት ፍቃደኛ ነኝ።
        - ➢ አድስ የሚመጡ ሃሳቦችን በመፅሀፍ ቅዱስ እውናት መሰረት በመፈተን አምናለሁ።
        - ➢ ሰው ስለቃሉ እውነት ቢቃወመኝ እንኳን ለቃሉ እውነት ለመቆምና ለማስተማሪ ፍቃደኛ ነኝ።
    - ማስተዋል የሚገቡን ነገሮች፡-
        - ➢ ከመፀሀፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ ነገር እንዳናስተምር መጠንቀቅ አለብን፣ ማመዛዘን አስፈላጊ ነው።
        - ➢ ሳይዘጋጁ ማስተማር ስጦታውን ያለአግባብ መጠቀም ነው። ለማስተማር መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።
        - ➢ ሰዎች ደስ የሚላቸውን ነገር ብቻ ማስተማር አይገባም።
        - ➢ ቃሉ የማይለውን መገለጥ አግንቻለሁ ብሎ ማስማር ተገቢ አይደለም።

*__ማጠቃለያ__*

- እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ - ከእግዚአብሔር የተሰጠንን የፀጋ ስጦታ ለክርስቶስ አካል መታነፅ ማዋል አለብን። ያለበለዚያ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እግዚአብሔር እንዳቀደው በሙላት አይሰራም፡፧
- እግዚአብሔር የሰጠንን የፀጋ ስጦታ ለጌታ አገልግሎት ካላዋልን - የእግዚአብሔር ሥራ በቤቱ በሙላት እንዳይሰራ ዕንቅፋት መሆናችን ነው።

በሚቀጥሉት ተከታታይ ጥናቶች - ሌሎችን የፀጋ ስጦታዎችን እንመለከታለን

ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።